# ከአገልግሎት ወይም የእርዳታ እንስሳዎት ጋር በመሆን ህይወትዎን ይቃኟት

የአሜሪካ የአካል ጉዳተኞች አዋጅ (ኤዲኤ - ADA) እና ፍትሃዊ የመኖሪያ ቤቶች ድንጋጌ (ኤፍኤችኤ - FHA) የአገልግሎት ወይም የእርዳታ እንስሳትን ለሚጠቀሙ የአካል ጉዳተኞች ጥበቃ እና መመሪያን ይሰጣሉ።

## ኤዲኤ

ኤዲኤ የአገልግሎት እንስሳ የሚለውን የአካል ጉዳት ላለበት ሰው ጥቅም ለመስጠት ስራ እንዲሰራ ወይም አገልግሎት እንዲሰጥ በግል የሰለጠነ ማንኛውም ውሻ ወይም ትንሽ ፈረስ ነው በማለት ይገልጸዋል።

## ኤፍኤችኤ

ኤፍኤችኤ የአገልግሎት እንስሳ የሚለውን የአካል ጉዳት ላለበት ሰው ጥቅም ለመስጠት ሲባል ስራ የሚሰራ፣ የሚያግዝ፣ ወይም አገልግሎቶችን የሚሰጥ ወይም የአንድን ሰው የአካል ጉዳት ሁኔታዎች ለማቃለል ስሜታዊ ድጋፍ የሚሰጥ ማንኛውም እንስሳ ነው በማለት ይገልጸዋል።

## መኖሪያ ቤት

በመኖሪያ ቤት ህንጻዎች ላይ፣ የአገልግሎት እንስሳትን ወደአከራይ ቢሮዎች ውስጥና ሌሎች የህዝብ መገልገያ ስፍራዎች ውስጥ ለመግባት እንዲችሉ ኤዲኤ መብት ይሰጣል።

በኤፍኤችኤ ድንጋጌ መሰረት፣ የእርዳታ እንስሳት በመኖሪያ ቤት ውስጥ እና በጋራ ቦታዎች ውስጥ ይፈቀዳሉ።

እንደ ኤፍኤችኤ ከሆነ፣ የመኖሪያ ቤት ህንጻው የቤት እንስሳትን የሚከለክል ከሆነ፣ የእነሱ የእርዳታ እንስሳት ከእነዚህ እገዳዎች ውጭ እንዲሆኑላቸው ባለቤቱ ምክንያታዊ የሆነ የማስተካከያ ጥያቄ ማቅረብ ይችላል። ጥያቄ ማቅረቢያው ግለሰቡ ያለበትን የአካል ጉዳት ሁኔታ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ (የአካል ጉዳቱ ማይታወቅ ወይም በቀላሉ የማይለይ ከሆነ) እና የእርዳታ እንስሳው በአካል ጉዳቱ ላይ እንዴት እገዛ እንደሚሰጣቸው ማብራራት አለበት።

## የህዝብ መገልገያዎች

በኤዲኤ ህግ መሰረት፣ የእርዳታ እንሰሳትን በማንኛውም የህዝብ መገልገያ ቦታዎች ማለትም፣ በምግብ ቤቶች፣ በመደብሮች፣ በሆስፒታሎች፣ እና ትምህርት ቤቶች ውስጥ ይዞ መግባት ይፈቀዳል።

በህዝባዊ ተቋማት ውስጥ የአገልግሎት እንስሳትን ይዞ ለመገኘት አስቀድሞ ማሳወቅ አያስፈልግም፣ እንስሳው በደንብ የሰለጠነ እና በባለቤቱ ቁጥጥር ስር የሆነ መሆን ብቻ ይጠበቅበታል።

## ይህን ያውቁ ነበር?

በእነዚህ ህጎች ስር የአገልግሎት እና የእርዳታ እንስሳት የእውቅና ማረጋገጫ እንዲኖራቸው አይጠበቅም። በተጨማሪም፣ ልብስ/ቬስት መልበስ ወይም ማንኛውንም ዓይነት መለያ ማንጠልጠል አይጠበቅባቸውም።

ሰንሰለት ወይም ልጓም ማድረግም አስፈላጊ አይደለም። የአገልግሎት እንስሳት የሚጠበቅባቸው ባለቤታቸው በሆነው ግለሰብ ቁጥጥር ስር መሆን ብቻ ነው።

equalrightscenter.org